# <u>የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የደንብ ልብስ አጠቃቀም መመሪያ …/2016</u>

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማት እንደተቋማቸው የሥራ ባህሪያት የራሳቸውን የሥራ ልብስ፣ የሥራ መሣሪያና ቁሳቁሶችን አጠቃቀም መመሪያ አዘጋጅተው መጠቀም እንዲችሉ በነሐሴ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በቁጥር መ.30/ጠ57/20/334 ከቀድሞው የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በተጻፈ ደብዳቤ በተሰጠው መመሪያ መሠረት የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በኢንስቲትዩቱ ዋና መስሪያ ቤትና በስሩ ላሉት የምርምር ማዕከላት እንደ ማዕከላቱ የሥራ ባህርይና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ የሚያገለግል የሥራ ልብስና የሥራ መሥሪያዎች አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የደንብ ልብስ አጠቃቀም መመሪያ …/2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

2.1 “የደንብ ልብስ” ማለት ኢንስቲትዩቱ ካለው የሥራ ባህርይ አንፃር ለልዩ ልዩ ዓይነት ሥራዎች ማከናወኛ የሚቀርብ የሥራ ልብስ ነው፡፡

2.2 ኢንስቲትዩት፡- ማለት የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማለት ነው፡፡

2.3 ፆታ፡- በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሁሉ የሴት ጾታንም የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

2.4 ለልዩ ልዩ ዓይነት ሥራዎች የሚሰጡት የሥራ ልብሶችና መሣሪያዎች ተለይተው የሚታወቁት ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት በተያያዙት ሠንጠረዦች ላይ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

2.5 የሥራ ልብስ እንዲሁም የሥራ መሣሪያ አጥኚ ቡድን ማለት በኢንስቲትዩቱ ለሚገኙ ሠራተኞች ለተሰማሩበት የሥራ ዓይነትና መደብ ተስማሚ የሥራ ልብስ እንዲሁም የሥራ

መሣሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው እያጠና እንዲቀርብ በተቋሙ የበላይ አካል በኩል የሚሰየም ከባለሙያዎች የተውጣጣ አጥኚ ቡድን ማለት ነው፡፡

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢንስቲትዩቱ ስር ተቀጥረው በሚሰሩ ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. ዓላማ

የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች በስራ ላይ ደህንነታቸውና ጤንነታቸው እንዲጠበቅ፣ ምቹ የስራ ሁኔታ እንዲፈጠር፣ የሥራ ዲስፕሊን እንዲጠበቅ እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ውጤታማነት ማሳደግ ነው፡፡

5. ለደንብ ልብስ የሚያገለግሉ የጨርቅ እና የጫማ ዓይነቶች

5.1 ካኪ ጨርቅ፡- ቀለሙ እንደተፈለገው ሆኖ መቶ በመቶ ከጥጥ የተሰራ ጨርቅ ማለት ነው፡፡

5.2 ቴትሮን ጨርቅ፡- ቀለሙ እንደተፈለገው ሆኖ ጨርቁ እንዳይጨማደድ ከሚረዳ ጥሬ ዕቃ የተዘጋጀ ጨርቅ ማለት ነው፡፡

5.3 አንድ ወጥ ኮትና ሱሪ፡- ከአንድ ዓይነት ፖሊስተር ወይም ፖሊስተር ካኪ ወይም ሱፍ ጨርቅ ወይም ቴትሮን ጨርቅ የሚዘጋጅ ሙሉ ልብስ ነው፡፡

5.4 ሸሚዝ፡- ቀለሙ እንደተፈለገው ሆኖ የፖሊስተር እና ከጥጥ ድብልቅ ወይም ሙሉ በሙሉ ከጥጥ ከተመረተ ጨርቅ የሚሰራ ነው፡፡

5.5 ቀሚስ፡- ቀለሙ እንደተፈለገው ዓይነት ሆኖ ሙሉ በሙሉ ከጥጥ ወይም ለቀሚስ አገልግሎት እንዲሆን ከተመረተ ጨርቅ የተሰራ ነው፡፡

5.6 ውስጥ ልብስ፡- ቀለሙ እንደተፈለገው ሆኖ ሙሉ በሙሉ ከጥጥ ወይም ለውስጥ ልብስነት ከሚያገለግል የጨርቅ ዓይነት የተሰራ ነው፡፡

5.7 ሽርጥ፡- ከጥጥ ወይም ከቆዳ ወይም ከፕላስቲክ ወይም ከሌላ ተስማሚ ጥሬ ዕቃ የተሰራ ሆኖ የልብስን መቆሸሽ ለመከላከል በልብስ ላይ ተደርቦ የሚለበስ ነው፡፡

5.8 ቱታ፡- ከጥጥ ወይም ከቴትሮን ወይም ባለ ክር ሴንቴቲክ ወይም ከካኪ ጨርቅ የተሰራና ሱሪው ከጃኬት ጋር ተያይዞ የተሰፋና የልብስን መቆሸሽ ለመከላከል በልብስ ላይ ተደርቦ የሚለበስ የስራ ልብስ ነው፡፡

5.9 የሱፍ ካፖርት፡- ከሱፍ ወይም ሙቀት እንዲሰጥ ገበር ያለውና ከጥጥ ወይም ድብልቅ ከሆነ ጥሬ ዕቃ የተሰራ ነው፡፡

5.10 የቆዳ ጃኬት፡- ከቆዳ የተሰራ ሆኖ ለሞተረኛ አገልግሎት ብቻ እንዲውል የሚያገለግል ባለገበር የልብስ ዓይነት ነው፡፡

5.11 ጋዋን ካፖርት (¾)፡- ነጭ ቀለም/ሰማያዊ ቀለም ሆኖ ከቴትሮን እና ከጥጥ ድብልቅ ጨርቅ የተሰራና በረዥም ኮትነት የተሰፋ የሥራ ልብስ ነው፡፡

5.12 የዝናብ ልብስ፡- ከሴንቴቲክ ብቻ የተሰራ ውሃ የማያስገባ የዝናብ መከላከያ ልብስ ነው፡፡

5.13 አጭር ቆዳ ጫማ፡- ማሰሪያ ያለው ወይም የሌለው ሆኖ ለቢሮ አካባቢ ስራ አገልግሎት የሚውልና ቁመቱ ከቁርጭምጭሚት የማያልፍ ከቆዳ የተሰራ ጫማ ነው፡፡

5.14 የወንድ ቆዳ ጫማ፡- አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ ሲሆን ዚፐር ወይም ማሰሪያ ያለው ሆኖ ለመስክ ስራ አገልግሎት የሚውልና ቁመቱ ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን ከቆዳ የተሰራ ጫማ ነው፡፡

5.15 የሴት ቆዳ ጫማ፡- አጭር ቡትስ ባለዚፐር ወይም ባለማሰሪያ ሆኖ ለሴቶች ለመስክ ሥራ የሚያገለግል ከቆዳ የተሰራ ጫማ ነው፡፡

5.16 ላስቲክ ቡትስ ጫማ፡- ከጎማ የተሰራ ገበር ያለው ሆኖ በክረምትና ጭቃ በሚበዛበት ወቅት የሚደረግና በቀላሉ የሚፀዳ ወይም የሚታጠብ ጫማ ነው፡፡

5.17 የንብ ማነቢያ ሙሉ ቱታ፡- ከባለ ክር ሴንቴቲክ ጥሬ ዕቃ የተሰራና ሙሉና አንድ ወጥ ሆኖ ከጭንቅላት እስከ እግር መሸፈን የሚችል በንብ ከመነደፍ የሚከላከል ልብስ ነው፡፡

5.18 የውኃ ዋና ትጥቅ፡- ከሴንቴቲክ ጥሬ ዕቃ የሚሠራ ሆኖ አንድ ወጥና ጭንቅላት በመሸፈን ውሃ እንዳያስገባ ለእጅ እንደ ጓንትና እግር እንዲሸፍን የሚያገለግል የውኃ ውስጥ ሕይወት ምርምር ላይ የሚሰማሩ ሠራተኞች የሚጠቀሙበት የሥራ ልብስ ነው፡፡

5.19 የላቦራቶሪ ጫማ፡- ነጠላ ጫማ ሆኖ ከፕላስቲክ የተሠራና ከፊት ለፊት ሽፍን የሆነ መጫሚያ ነው፡፡

5.20 ሴፍቲ ሹዝ (የደህንነት ጫማ)፡- አፍንጫው ብረት ለበስ ቆዳ ሆኖ በብረታ ብረት ወርክ ሾፕ ወይም በተሽከርካሪዎች ጋራዥ ለሚያጋጥሙ አደጋዎች መከላከያ የሚለበስ ጫማ ነው፡፡

6. የደንብ ልብስ የሚሰጥበት ሁኔታ

6.1 የደንብ ልብስ በተፈቀደበት የሥራ መደብ ላይ የተመደበ ማንኛውም ሠራተኛ ለሥራውና ለሠራተኛው ደህንነት ሲባል የደንብ ልብስ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

6.2 ከላይ በተራ ቁጥር 6.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙን በማንኛውም ሁኔታ የለቀቀ ሠራተኛ የሰራበትን ጊዜና ያልተሰጠውን ጊዜ በመጥቀስ ወደ ኋላ (ውዝፍ) የደንብ ልብስ መጠየቅ አይችልም፡፡

6.3 በጡረታ ወይም በሞት ምክንያት ኢንስቲትዩቱን የለቀቀ ሰራተኛ ቢያንስ የግማሽ ዓመት አገልግሎት ከሰጠ ለሰራበት ጊዜ ታስቦ የደንብ ልብስ ይሰጠዋል፡፡

6.4 በረጅም ጊዜ ትምህርት፣ ያለ ደመወዝ ፈቃድ፣ በትውስት ወይም በጊዜያዊነት ወደ ሌላ መስሪያ ቤት የተዛወረ ሰራተኛ በመደበኛ የሥራ ገበታው ላይ ያልተገኘ ሰራተኛ በሥራ ልብስና መሳሪያ ዕደላው አይካተትም፡፡

7. የሠራተኛው ግዴታ

የደንብ ልብስ የተሰጠው ሠራተኛ፡-

7.1 የተሰጠውን የደንብ ልብስ አሟልቶ በሥራ ላይ የመልበስ ግዴታ አለበት፤

7.2 ሠራተኛው ስለ አደጋ መከላከያ እርምጃዎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰውን እንዲሁም በአንቀጽ 66 የተደነገገውን የመንግሥት ሠራተኞች ግዴታና የሥነ ምግባር መመሪያዎች የማክበርና የመፈጸም ግዴታ ይኖርበታል፡፡

8. የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ

በዚህ መመሪያ መሰረት የሚከተሉትን ተግባራት የፈፀመ ሰራተኛ በዲስፕሊን ተጠያቂ ይሆናል፤

8.1 የደንብ ልብስ የተሰጠው ሰራተኛ ከላይ በተራ ቁጥር 7 ላይ የተጣለበትን ግዴታ በአግባቡ ካልፈፀመ፣

8.2 የተጠቀሱትን የደንብ ልብሶች በዚህ መመሪያዎች ከተፈቀደላቸው ሰራተኞች ውጭ የሰጠ ባለሙያ/ኃላፊ፣

8.3 የተሰጠውን የደንብ ልብስ የሸጠ ወይም ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ፣

8.4 የተሰጠውን የደንብ ልብስ ከተፈቀደለት የሥራ ቦታ ውጭ ከለበሰ፣

8.5 የተሰጠውን ደንብ ልብስ በንጽህና ያልያዘ፣

8.6 ሰራተኛው የደንብ ልብስ መሳሪያውን በአግባቡ እንዲጠቀም ባለመቆጣጠሩ ለሚፈጠሩ ችግሮች የሚመለከተው ኃላፊ በመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1046/2011 አንቀጽ 69 እና 70 በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## 9. የመመሪያው አተገባበር

9.1 በበጀት ዓመቱ ለተቋሙ በተፈቀደው የደንብ ልብስ በጀት መሰረት በአጠቃላይ የሚያስፈልገው የደንብ ልብስ ዕቅድ በመሰረታዊ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ ይዘጋጃል፤

9.2 የአንድ የበጀት ዓመት ደንብ ልብስ አቅርቦት እና ዕደላ ከግማሽ ዓመት ማብቂያ በፊት መከናወን ይኖርበታል፤

9.3 ማንኛውም የደንብ ልብስ ዕደላ የሚከናወነው በዋና መስሪያ ቤት ወይም በማዕከላት በዕቃ ግምጃ ቤት በኩል ይሆናል፡፡

9.4 በዚህ መመሪያ መሠረት የደንብ ልብስ በሚያስፈልጋቸው የሥራ መደቦች ላይ ለሚሰሩ ሠራተኞች የሚሰጠው የደንብ ልብስ ግዥ ከመፈፀሙ በፊት በተወካዮች አማካይነት መረጣ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡

## 10. መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ኢንስቲትዩቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን የደንብ ልብስ አጠቃቀም መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 11. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊ ከፀደቀበት ከ _____ ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

--------------------- **ዋና**

**ዳይሬክተር**

**የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት**

## 12. የደንብ ልብስ የተፈቀደላቸው የሥራ መደቦች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀደ የደንብ ልብስ | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ |
|---|---|---|---|
| 1. | ተመራማሪ | • ¾ ነጭ ጋዋን/ቴትሮን/ በዓመት 1<br>• አጭር ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 1<br>• ፕላስቲክ ቦት ጫማ በሁለት ዓመት 1<br>• ካኪ ቱታ በዓመት 1 (ለእንስሳት ተመራማሪዎች)<br>• ሴፍቲ ጫማ በዓመት 1 (ለግብርና ምህንድስና ተመራማሪዎች)<br>• ሰማያዊ ቴትሮን ቱታ፣ ጃንጥላ በዓመት 1 (ለእንስሳት ህክምና ተመራማሪዎች)<br>• የዝናብ ልብስ በሁለት ዓመት 1 (ለንብ ተመራማሪዎች)<br>• የላቦራቶሪ ጫማ (ለቲሹ ካልቸር ሠራተኛ) በዓመት 1 | • የእጅ ጓንት ፕላስቲክ<br>• የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ<br>• የአይን መነጽር (ጎግል)<br>• UV Protective<br>• የላቦራቶሪ ውስጥ የጨርቅ ቆብ<br>• ፌስሺልድ/የፊት ጭምብል አይን መነጽር/<br>• ሙሉ ሽርጥ ፕላስቲክ እጅ ድረስ የሚሸፍን<br>• የንብ አናቢ ቱታ<br>• የውሃ መዋኛ ልብስ<br>• የላይፍ ሴቨር ጃኬት |
| 2. | • የላብራቶሪ ቴክኖሎጂስት፣<br>• የላብራቶሪ ምርምር ረዳት<br>• የላቦራቶሪ ካስቶዲያን<br>• የኬሚካል ላብራቶሪ ፍተሻ ባለሙያ<br>• የቴክኒክ ረዳት<br>• የላብራቶሪ አቴንዳንት | ¾ ነጭ ጋዋን/ካኪ/በዓመት 2<br>አጭር ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | • የጨርቅ ቆብ<br>• ሙሉ ፕላስቲክ ሽርጥ<br>• የአይን መነጽር/ጎግልስ<br>• የላቦራቶሪ ሴፍቲ ጫማ<br>• የአፍና አፍንጫ ማስክ<br>• የእጅ ጓንት (ፕላስቲክ)<br>• ሸሚዝ /ሰማያዊ በዓመት 1 ከኬሚካል ጋር ግንኙነት ላላቸው |
| 3. | የመስክ ምርምር ረዳት | • ሰማያዊ ቴትሮን ቱታ በዓመት 1<br>• ፕላስቲክ ቦት ጫማ በዓመት 1<br>• አጭር ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 1<br>• ሸሚዝ በዓመት 1 | • የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ<br>• የፕላስቲክ ጓንት<br>• የመስክ የኬሚካል ኮፍያ<br>• የፕላስቲክ ቱታ ውስጠ ክር |

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀደ የደንብ ልብስ | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ |
| --- | --- | --- | --- |
| | | የዝናብ ልብስ በሁለት ዓመት 1 | • ጃንጥላ<br>• ጎግልስ |
| 4. | • የእንስሳት አዳቃይ ቴክኒሽያን፣<br>• ረዳት የእንስሳት ሀኪም፣<br>• የእንስሳት መኖ ዝግጅትና ቅንብር ባለሙያ | • ሰማያዊ ቴትሮን ቱታ በዓመት 1<br>• አጭር ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 1<br>• ፕላስቲክ ቦት ጫማ በዓመት 1<br>• የዝናብ ልብስ በሁለት ዓመት 1 | • ፕላስቲክ የእጅ ጓንት<br>• የአፍና የአፍንጫ ማስክ<br>• ፕላስቲክ ሙሉ ሽርጥ እጅን የሚሸፍን |
| 5. | ሜትሮሎጂካል ፎርካስቲንግ ቴክኒሽያን | ነጭ ቴትሮን ጋዋን በዓመት 1<br>አጭር ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 1<br>ፕላስቲክ ቦት ጫማ በዓመት 1 | ጃንጥላ  የፀሐይ<br>መከላከያ ባርኔጣ |
| 6. | • የቴክኖሎጂ ብዜት እና እርሻ አያያዝ<br>• የምርት ጥራት ባለሙያ<br>• የእርሻ መሳሪያዎች ቡድን መሪ | ነጭ ¾ ጋዋን ቴትሮን በዓመት 1<br>አጭር ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 2<br>ፕላስቲክ ቦት ጫማ በዓመት 1<br>የዝናብ ልብስ በሁለት ዓመት 1 | • የመስክ ባርኔጣ ክብ ከካኪ የተሰራ<br>• ፕላስቲክ ጓንት፤<br>• የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ፤<br>• ጃንጥላ |
| 7. | የእርሻ መሣሪያዎች ኦፕሬተር | • ሰማያዊ ካኪ ቱታ በዓመት 2<br>• ሸሚዝ በዓመት 2<br>• አጭር ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 2<br>• ፕላስቲክ ቦት ጫማ በዓመት 1<br>• የዝናብ ልብስ በሁለት ዓመት 1<br>• ከካኪ ጨርቅ የተሠራ ጆሮ የሚሸፍን ቆብ በዓመት 2<br>• ከቴትሮን ጨርቅ የተሠራ ጆሮ የሚሸፍን ቆብ በዓመት 2 (ለቆላማ አካባቢዎች) | • የሹራብ/ሸራ ጓንት<br>• የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ<br>• የዓይን መነፅር(ጎግል)፤<br>• የአቧራ መከላከያ መነጽር ባለማሰሪያ<br>• ባለ ክር ሲንቴቲክ ቱታ የኬሚካል ርጭት ላይ ለሚሰራ ብቻ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8. | ሁለገብ የምርምር ድጋፍ | ሰማያዊ ካኪ ቱታ በዓመት 2 | የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ |

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀደ የደንብ ልብስ | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ |
|---|---|---|---|
| | ሰጭ ሠራተኛ | • ሰማያዊ ቴትሮን ቱታ በዓመት 2 (ለቆላማ አካባቢ)<br>• አጭር ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 2<br>• ሸሚዝ በዓመት 2<br>• ፕላስቲክ ቦት ጫማ በዓመት 1<br>• የዝናብ ልብስ በሁለት ዓመት 1 | • የእጅ ጓንት የሸራ<br>• ሴንቴቲክ ቱታ ክር ያለው ኬሚካል ላይ ለሚሰሩ ብቻ<br>• ጎግልስ<br>• የጨርቅ ቆብ<br>• ጃንጥላ |
| 9. | የህግ ባለሙያዎች | ሙሉ ልብስ በዓመት 1 | |
| 10. | • የጥበቃ ተቆጣጣሪ<br>• የጥበቃ ሰራተኛ (ወንድ) | • ለኮትና ሱሪ የሚሆን ቴትሮን ጨርቅ በዓመት 2 (አንድ የተሰፋ፤ አንድ ብትን)<br>• ሸሚዝ በዓመት 2<br>• አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ በዓመት 2<br>• የሱፍ ካፖርት በ4 ዓመት 1 | • ጃንጥላ በሁለት ዓመት 1<br>• የሹራብ ጓንት<br>• የዝናብ ልብስ በሁለት ዓመት 1 |
| 11. | • የጥበቃ ተቆጣጣሪ<br>• የጥበቃ ሰራተኛ (ሴት) | • ለኮትና ሱሪ የሚሆን ቴትሮን ጨርቅ በዓመት 2 (አንድ የተሰፋ፤ አንድ ብትን)<br>• ውስጥ ልብስ በዓመት 1<br>• ሸሚዝ 1<br>• አጭር ጉርድ ቆዳ ጫማ በዓመት 2 | • የሹራብ ጓንት<br>• ዝናብ ልብስ በሁለት ዓመት 1<br>• ጃንጥላ በሁለት ዓመት 1 |
| 12. | የቢሮ ረዳት<br>• ወንድ<br><br>• ሴት | ኮትና ሱሪ ጨርቅ ቴትሮን/ፖሊስተር በዓመት 2<br>(አንድ የተሰፋ፤ አንድ ብትን)<br>ሸሚዝ በዓመት 2<br>አጭር ቆዳ ጫማ በዓመት 2 የወንድ<br>ጃንጥላ በሁለት ዓመት 1 ክራቫት<br>በዓመት ከቴትሮን የሚሰፋ 2<br>የጨርቅ ቆብ በዓመት 2 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ኮትና ጉርድ ቀሚስ በዓመት 2<br>አንድ ወጥ ሸሚዝና ሱሪ በዓመት 1 (አንድ የተሰፋ፤ | |

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀደ የደንብ ልብስ | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ |
|---|---|---|---|
| | | አንድ ብትን) ሸሚዝ የሴት በዓመት<br>1 የውስጥ ልብስ የሴት በዓመት 1<br>አጭር ቆዳ ጫማ በዓመት 2 የሴት<br>ክራቫት ከቴትሮን የሚሰፋ በዓመት<br>2 የጨርቅ ቆብ በዓመት 2 | |
| 13. | የፅዳት ሰራተኛ<br>• ወንድ<br><br>• ሴት | ኮትና ሱሪ ጨርቅ ቴትሮን/ፖሊስተር በዓመት 2<br>(አንድ የተሰፋ፤ አንድ ብትን)<br>ሸሚዝ በዓመት 2<br>አጭር ቆዳ ጫማ በዓመት 2 የወንድ<br>ጃንጥላ በሁለት ዓመት 1<br>የጨርቅ ቆብ በዓመት 2<br><br>ኮትና ጉርድ ቀሚስ በዓመት 2<br>አንድ ወጥ ሸሚዝና ሱሪ በዓመት 1 (አንድ የተሰፋ፤<br>አንድ ብትን) ሸሚዝ የሴት በዓመት 1 የውስጥ ልብስ<br>የሴት በዓመት 1 አጭር ቆዳ ጫማ በዓመት 2 የሴት<br>የጨርቅ ቆብ በዓመት 2 | ከፕላስቲክ የተሰራ ሙሉ<br>ቱታ ውስጠ ክር የእጅ ጓንት<br>ፕላስቲክ<br>የአይን መነጽር/ጎግል/፤ UV Protective<br>የጨርቅ ቆብ<br>የአፍና አፍንጫ ማስክ በትነት መልክ<br>ኬሚካል የማያስገባ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 14. | ፖስተኛ/በሞተር ሳይክል/ | አንድ ወጥ ቴትሮን/ፖሊስተር ሱሪና ሸሚዝ ወጥ በዓመት 2 (አንድ የተሰፋ፤ አንድ ብትን) አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ በዓመት 2 የዝናብ ልብስ በሁለት ዓመት 1 ሄልሜት ፎርማይካ/ቆብ በ5 ዓመት 1 | |

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀደ የደንብ ልብስ | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ |
|---|---|---|---|
| | | ጓንት የሹራብ በዓመት 1<br>የቆዳ ጃኬት በ4 ዓመት 1 | |
| 15. | የግቢ ውበትና መናፈሻ አስተባባሪ | ሰማያዊ ካኪ ጋወን በዓመት 1 አጭር ቦትና የቆዳ ጫማ በሁለት ዓመት 1<br>የወንድ ላስቲክ ቦት ጫማ በዓመት 1 | |
| 16. | የግቢ ውበትና መናፈሻ ሠራተኛ | ሰማያዊ ካኪ ቱታ በዓመት 2 ቴትሮን/ፖሊስተር ኮትና ሱሪ በዓመት 1 (ብትን) ሸሚዝ በዓመት 2 አጭር ቦትና የቆዳ ጫማ በዓመት 2 የወንድ ላስቲክ ቦት ጫማ በዓመት 1 ባለጆሮ መሸፈኛ ኮፍያ በዓመት 2 | የአፍና አፍንጫ ማስክ ሰንቲቲክ ቱታ ከነኮፍያው የፕላስቲክ ጓንት የመሳሰሉት እንደአስፈላጊነቱ እየተገዛ በኬሚካል ርጭት ጊዜ ብቻ የሚጠቀሙበት ይሰጣል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 17. | አትክልተኛ<br>• ወንድ<br><br>• ሴት | ሰማያዊ ካኪ ቱታ በዓመት 2 ቴትሮን/ፖሊስተር ኮትና ሱሪ በዓመት 1 (ብትን) ሸሚዝ በዓመት 2 አጭር ቦትና የቆዳ ጫማ በዓመት 2 የወንድ ላስቲክ ቦት ጫማ በዓመት 1 ባለጆሮ መሸፈኛ ኮፍያ በዓመት 2 | የአፍና አፍንጫ ማስክ ሰንቲቲክ ቱታ ከነኮፍያው የፕላስቲክ ጓንት የመሳሰሉት እንደአስፈላጊነቱ እየተገዛ በኬሚካል ርጭት ጊዜ ብቻ የሚጠቀሙበት ይሰጣል |

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀደ የደንብ ልብስ | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ |
|---|---|---|---|
| | | ሰማያዊ ካኪ ቱታ በዓመት 2 አንድ ወጥ ሸሚዝና ሱሪ በዓመት 1(ብትን) ሸሚዝ የሴት በዓመት 2 አጭር ቦትና የቆዳ ጫማ በዓመት 2 የሴት ላስቲክ ቦት ጫማ በዓመት 1 ባለጆሮ መሸፈኛ ኮፍያ በዓመት 2 | የአፍና አፍንጫ ማስክ ሰንቲቲክ ቱታ ከነኮፍያው የፕላስቲክ ጓንት የመሳሰሉት እየተገዛ እንደአስፈላጊነቱ በኬሚካል ርጭት ጊዜ ብቻ የሚጠቀሙበት ይሰጣል |
| 18. | የንብረት ምዝገባ ሠራተኛ<br>• ወንድ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 አጭር ቦትስ ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | የእጅ ጓንት /ሸራ/ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ /ማስክ/ |
| | • ሴት | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 የሴት ጉርድ ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | የእጅ ጓንት /ሸራ/ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ /ማስክ/ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 19. | የንብረት ባለሞያ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 አጭር<br>ቦትስ ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | የእጅ ጓንት /ሸራ/ የአፍና<br>የአፍንጫ መሸፈኛ /ማስክ/ |
| 20. | የዕቃ ግ/ቤት ኃላፊ<br>• ወንድ | ሰማያዊ ካኪ ቱታ በዓመት 1 ሰማያዊ<br>¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 2 አጭር<br>ቦትስ ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | የእጅ ጓንት /ሸራ / የአፍና<br>የአፍንጫ መሸፈኛ /ማስክ/ |
| | • ሴት | ሰማያዊ ካኪ ቱታ በዓመት 1 ሰማያዊ<br>¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 2 ቆዳ<br>ጫማ የሴት በዓመት 1 | የእጅ ጓንት /ሸራ / የአፍና<br>የአፍንጫ መሸፈኛ /ማስክ/ |

| ተ. ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀደ የደንብ ልብስ | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ |
|---|---|---|---|
| 21. | ሁለገብ የጥገና ሠራተኛ<br>• ወንድ | ሰማያዊ ካኪ ቱታ በዓመት 2<br>ሸሚዝ በዓመት 2 ቆዳ ጫማ<br>ጉርድ ቡትስ በዓመት 2 ላስቲክ<br>ቦት ጫማ በዓመት 1 ሴፍቲ<br>ጫማ በዓመት 1 | የእጅ ጓንት /ሸራ / የአፍና<br>የአፍንጫ መሸፈኛ /ማስክ/ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | • ሴት | ሰማያዊ ካኪ ቱታ በዓመት 2<br>ሸሚዝ በዓመት 2 ቆዳ ጫማ<br>ጉርድ ቡትስ በዓመት 2 ላስቲክ<br>ቦት ጫማ በዓመት 1 ሴፍቲ<br>ጫማ በዓመት 1 | |
| 22. | ኤሌክትሪሽያን/የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ቴክኒሻን<br>• ወንድ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1<br>ሰማያዊ ቴትሮን/ፖሊስተር ቱታ በዓመት 1<br>ሸሚዝ በዓመት 1 አጭር ቦትስ ቆዳ ጫማ<br>በዓመት 2 | የእጅ ጓንት<br>/ሽራ / |
| | • ሴት | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1<br>ሰማያዊ ቴትሮን ቱታ በዓመት 1 ሸሚዝ<br>በዓመት 1 | የእጅ ጓንት /ሽራ / |

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀደ የደንብ ልብስ | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ |
|---|---|---|---|
| | | አጭር ጉርድ ቡትስ የሴት ቆዳ ጫማ በዓመት 2 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 23. | አውቶ ኤሌክትሪሺያን<br>• ወንድ | አጭር የወንድ ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 1 ሴፍቲ ጫማ በዓመት 1 ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 ሰማያዊ ቴትሮን ቱታ በዓመት 1 ሸሚዝ በዓመት 1 | የእጅ ጓንት ፕላስቲክ የአይን መከላከያ ጎግልስ የአሲድ መከላከያ ፕላስቲክ ሙሉ ወጥ<br>ሽርጥ<br>የአፍንጫ ማስክ |
| | • ሴት | አጭር የሴት ቆዳ ጫማ በዓመት 1 ሴፍቲ ጫማ በዓመት 1 ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 ሰማያዊ ቴትሮን ቱታ በዓመት 1 ሸሚዝ በዓመት 1 | |
| 24. | የግብርና መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች ጥገና ባለሙያ<br>ወንድ | አጭር የወንድ ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 1 ሴፍቲ ጫማ በዓመት 1 ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 ሰማያዊ ቴትሮን ቱታ በዓመት 1 ሸሚዝ በዓመት 1 | የአይን አደጋ መከላከያ<br>ጎግልስ ጓንት የቆዳ የቆዳ<br>ሙሉ ሽርጥ |

| ተ. ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀደ የደንብ ልብስ | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ |
|---|---|---|---|
| | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሴት | አጭር የሴት ቆዳ ጫማ በዓመት 1<br>ሴፍቲ ጫማ በዓመት 1 ሰማያዊ ¾<br>ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 ሰማያዊ<br>ቴትሮን ቱታ በዓመት 1 ሸሚዝ<br>በዓመት 1 | |
| 25. | የተሽከርካሪ ጥገና ባለሙያ | ሰማያዊ ቴትሮን ቱታ በዓመት 2 አጭር<br>ቦትስ ቆዳ ጫማ በዓመት 2 ሸሚዝ<br>በዓመት 1 | የአይን አደጋ መከላከያ ጎግልስ<br>ጓንት የቆዳ የቆዳ ሙሉ ሽርጥ |
| 26. | አውቶ መካኒክስ | አጭር የወንድ ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 1<br>ሴፍቲ ጫማ በዓመት 1 ሰማያዊ ¾<br>ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 ሰማያዊ<br>ቴትሮን ቱታ በዓመት 1 ሸሚዝ በዓመት<br>1 | የአይን አደጋ መከላከያ ጎግልስ<br>ጓንት የቆዳ የቆዳ ሙሉ ሽርጥ |
| 27. | የብየዳ ባለሙያ | አጭር የወንድ ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 1<br>ሴፍቲ ጫማ በዓመት 1 ሰማያዊ ¾<br>ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 ሰማያዊ<br>ቴትሮን ቱታ በዓመት 1 ሸሚዝ በዓመት<br>1 | የአይን አደጋ መከላከያ ጎግልስ<br>ጓንት የቆዳ የቆዳ ሙሉ ሽርጥ |
| 28. | ጎሚስታና መኪና አጣቢ | ሰማያዊ ካኪ ቱታ በዓመት 2 አጭር<br>ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | ጓንት ከፕላስቲክ የተሰራ የአፍና<br>አፍንጫ መሸፈኛ/ማስክ |
| ተ. ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀደ የደንብ ልብስ | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ፕላስቲክ ቦት ጫማ በዓመት 1<br>ሽሚዝ በዓመት 1 | |
| 29. | ነዳጅ ዘይትና ቅባት አዳይ | ሰማያዊ ካኪ ቱታ በዓመት 1 ሽሚዝ<br>በዓመት 1 ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት<br>በዓመት 1 አጭር  ቡትስ ቆዳ ጫማ<br>በዓመት 2 | ማስክ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ<br>ሽራ ጓንት የጨርቅ ቆብ<br>ፕላስቲክ ቦት ጫማ |
| 30. | የተሽከርካሪ ስምሪት ባለሙያ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1<br>አጭር  ቡትስ ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | |

| ተ.ቁ. | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ተፈላጊ የሥራና የደንብ ልብስና የስራ መሣሪያዎች | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ (Protection) |
|---|---|---|---|
| 31. | ሾፌር<br>• ወንድ | ኮትና ሱሪ ቴትሮን በዓመት 2<br>(አንድ የተሰፋ፤ አንድ ብትን)<br>ሰማያዊ ቴትሮን ቱታ በዓመት 1<br>ሸሚዝ በዓመት 2 ቆዳ ጫማ<br>አጭር ቦት በዓመት 2 የዝናብ<br>ልብስ በሁለት ዓመት 1 | |
| | • ለሴቶች | ኮትና ቀሚስ ቴትሮን/ፖሊስተር በዓመት 2<br>(አንድ የተሰፋ፤ አንድ ብትን)<br>ሰማያዊ ቴትሮን ቱታ በዓመት 1<br>ሸሚዝ በዓመት 2 የሴት ቆዳ<br>ጫማ በዓመት 2 የዝናብ ልብስ<br>በሁለት ዓመት 1 | |
| 32. | የስልክ ኦፕሬተሮች<br>• ወንድ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 1 | |
| | • ሴት | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 1 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 33. | ፎቶ ኮፒ ማባዣና ህትመት ሠራተኛ<br>ወንድ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 2<br>ቆዳ ጫማ አጭር ቡትስ በዓመት 1<br>የጨርቅ ቆብ በዓመት 1 | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ/ማስክ የዕጅ ጓንት ፕላስቲክ፤ የፊት መሸፈኛ/ፌስሺልድ |
| | /ሴት | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 2 ቆዳ ጫማ አጭር ቡትስ በዓመት 1 የጨርቅ ቆብ በዓመት 1 | የአይን መነጽር/ጎግልስ |

| ተ. ቁ. | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ተፈላጊ የሥራና የደንብ ልብስና የስራ መሣሪያዎች | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ (Protection) |
|---|---|---|---|
| 34. | የኮምፒውተር ጥገና ባለሙያ/ቴክኒሻን | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 1 | |
| 35. | የቤተመጽሐፍት ሠራተኞች | ነጭ ¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 1 | |
| 36. | የዕቃ ግዥ ባለሙያና ሠራተኛ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 1 | |
| 37. | የሂሳብ ሰነድ ያዥ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 1 | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ/ማስክ<br>የፊት መሸፈኛ/ፌስሺልድ |
| 38. | የሪከርድና ማህደር ሠራተኛ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 1 | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ/ማስክ<br>የፊት መሸፈኛ/ፌስሺልድ |
| 39. | የመረጃ ዴስክ ሠራተኛ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 | |
| 40. | የጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ<br>• ወንድ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋዋን በዓመት 1 አጭር ቦት ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | |
| | • ሴት | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋዋን በዓመት 1 አጭር ቦት ቆዳ ጫማ የሴት በዓመት 1 | |
| 41. | የፕሮቶኮል ባለሙያ<br>ወንድ | ሙሉ ልብስ በዓመት 2 ሸሚዝ በዓመት 2 | ዣንጥላ |

| ተ. ቁ. | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ተፈላጊ የሥራና የደንብ ልብስና የስራ መሣሪያዎች | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ (Protection) |
|---|---|---|---|
| | ሴት | ጉርድ ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | |
| | | ሙሉ ልብስ በዓመት 2<br>ሸሚዝ በዓመት 2 ጉርድ<br>ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | |
| 42. | አዶቪዥዋል ቴክኒሻን | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋዋን በዓመት 1<br>አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | የፀሐይ መከላከያ ኮፍያ<br>ክብ ጃንጥላ |
| 43. | ሲቪል መሀንዲስ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋወን በዓመት 1 | |
| 44. | የካፌቴሪያ ወጥ ቤት ሠራተኛ እና አስተናጋጅ | የጨርቅ ቆብ በዓመት 2 በቁልፍ<br>ተካፋች ቀሚስ በዓመት 2<br>ሰደሪያና ሱሪ በዓመት 2 የቆዳ<br>ጫማ ለሴት በዓመት 2 የቆዳ<br>ጫማ ለወንድ በዓመት 2 ሽርጥ<br>በዓመት 2 | |
| 45. | የካፌቴሪያ ባሬስታ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋዋን በዓመት 2<br>አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | |
| 46. | የካፍቴሪያ የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ አስተናጋጅ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ጋዋን በዓመት 2<br>አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 47. | ካፊቴሪያ የሂሳብ ሠራተኛና | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 | |
| ተ. ቁ. | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ተፈላጊ የሥራና የደንብ ልብስና የስራ መሣሪያዎች | በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች መከላከያ (Protection) |
| | አስተናጋጅ | | |
| 48. | የካፊቴሪያ ገንዘብ ያዥ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 | |
| 49. | የካፊቴሪያ የግዥ ሠራተኛና አስተናጋጅ | ሰማያዊ ¾ ቴትሮን ካፖርት በዓመት 1 | |
| 50. | የእንጀራና የዳቦ ጋጋሪ | የጨርቅ ቆብ በዓመት 2 ሙሉ<br>ሸርጥ በዓመት 2 አጭር ቡትስ<br>ቆዳ ጫማ በዓመት 1 | |
| 51. | የካፊቴሪያ አስተናጋጅ | ነጭ ¾ ቴትሮን ጋዋን በዓመት 2<br>የጨርቅ ቆብ በዓመት 2 | |
| 5 | የወጥ ቤት ጽዳት ሠራተኛ | ቴትሮን ጉርድ ቀሚስና ኮት በዓመት<br>1 የሴት ቆዳ ጫማ በዓመት 1 ሸሚዝ<br>የሴት በዓመት 1 ውስጥ ልብስ<br>በዓመት 1 ላስቲክ ቦት ጫማ የሴት<br>በዓመት 1 የጨርቅ ቆብ በዓመት 2<br>ሙሉ ሸርጥ እጅጌ ያለው በዓመት 2 | |